# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው - ሕዝብ

(ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር፣)

መብትና ጥቅም

የሚታገል ጋዜጣ

መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)

All ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (ME'ISONE)

P. O. Box 3198 . 10364 Stockholm 3 . Sweden . e-mail: meisone@t-online.de

| ዓመት | ቁጥር |
|---|---|


# ሙሉጌታ ሃይሉ

## ጓዳችን፣ ወንድማችን፣ ሙሉ ሰው

ወንድማችን ሙሉጌታ ሃይሉ ግንቦት 1 ቀን 2004 ዓ.ም በድንገት ከዚህ አለም በሞት መለየቱን ስንሰማ እኛ የመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች የተሰማንን ሃዘንና ድንጋጤ በቃላት መግለፅ አንችልም። ከለጋ ወጣትነት ዘመኑ አንስቶ በቅድመ አብዮቱ ዘመን በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ከዚያም የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መኢሶን/ አባል በመሆን ከአርባ አመታት በላይ ለዚች አገራችን የተሻለ ቀን ለማምጣት በሚደረገው ትግል ሰለቸኝ፣ መረረኝ፣ ደከመኝ ሳይል ህይወቱን ሲሰዋ የቆየ ፅኑ ጓዳችንና ወንድማችን ነበር። ይህ ያሳሰለሰ ልፋቱ ከግቡ ሳይደርስ፣ ለሚወዳት አገራችን የነበረው ራእይ ገና እውን ሳይሆን ከዚህ አለም በሞት መለየቱ ሃዘናችንን እጥፍ ድርብ አድርጎታል። ይህም ሆኖ ወንድማችን ሙሉጌታ አራት አስርት አመታት ባስቆጠረው የትግል ታሪኩ ጥሎልን ያለፈውን የቅን ታጋይ አርአያነት አንግበን ከተጓዝን ይህንን ህልሙን እውን ከማድረግ የሚያግደን ምንም ነገር አይኖርም በሚለው እምነታችን እንፅናናለን።

ይህ የትግል አርአያነት ደግሞ በፅናት ገፅታው ብቻ የሚወሰን አይደለም። ሙሉጌታ የሚለውን ለማወቅ የማይታክት አንባቢ፣ በአቋሙና እምነቱ ሳይታጠር፣ ፅናትንና ክፍተትን ሳያምታታ የሌሎችን አስተሳሰብ ለመረዳት ክፍት በሆነ ህሊና ተወያይና አድማጭ፣ በኛ ባህልና ህብረተሰብ ቀርቶ በዴሞክራሲያዊ አገሮች እንኳን በማይታይ ደረጃ ይህ ነው የማይባል የመቻቻል ባህል ያዳበረና በግል ህይወቱ ለነገይቱ አዲስ ኢትዮጵያችን ያለውን ህልም ከወዲሁ እውን አድርጎ የሚኖር ታላቅ ዴሞክራትና አገር ወዳድ ዜጋ ነበር።

በዚህ ረጅም የትግል ጉዞው ሙሉጌታ ከሁሉም ከሁሉም የደከመበት አንድ አላማ ለኢትዮጵያቺን በተያዘው ታሪካዊ ተጋድሎ የዚች አገር ዴሞክራቶች የትግል አንድነት ጉዳይ ነበር። በደርግ ዘመን ከተፈጠረው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ቅንጅት (ኢዴሃቅ) አንስቶ ከዚያም ፓሪስ አንድንና የግዮን ጉባኤን ተከትሎ የተቋቋመው አማራጭ ሃይሎች፣ ከፓሪስ ሁለት በኋላ ኢተፖድህ፣ ከዚያም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት (ኢዴሃህ) ሲቋቋሙ "ልዩነት ተከብሮ አንድነት" በሚል መርህ የሙሉጌታ ገንቢ እጅ የሌለባቸው የመሰባሰብ ጥረቶች አልነበሩም።

የወንድማችን የሙሉጌታ ህይወት በፖለቲካው አለም የታጠረ አልነበረም። ሙሉጌታ ትግል ሲባል ታጋይ፣ ፅናት ሲባል ፅኑ፣ ወዳጅ ሲባል ቁም ነገረኛና ለዛ ያለው ተጫዋች፣ እናት አባት ወንድም እህት ልጅ ሲባል ወሰን የሌለው የቤተሰብ ፍቅር የተሳበሰ ሙሉ ሰው ነበር። ከዚህም በመነሳት ዛሬ በዚች የፈተና ወቅት ለእህቶቹና ወንድሞቹ እነሱ ብቻ ሳይሆኑ እኛም እንደነሱ ወንድማችንን፣ ለልጁ ለታየ እኛም እንደ እሱ አፍቃሪና መካሪ አባታችንን፣ በትግሉ ሜዳ ለዚች አገር በጎ ራእይ አንግበው እንደሱ ሲንቀሳቀሱ ለተገናኙት ስፍር ቁጥር የሌላቸው ወገኖች እኛም እንደነሱ የትግል አጋራችንን ያጣን መሆናችንንና ሃዘናቸው ሃዘናችን መሆኑን እያረጋገጥን ለሁላችንም ፅናቱን ይስጠን እንላቸዋለን።

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን)
ግንቦት 2 ቀን 2004 አ.ም.